# የቅድስት ሥላሴ ዩኒቨርሲቲ
# የርቀት ትምህርት ኮሌጅ

## Holy Trinity University

College of Distance and E-Learning Education

Addis Ababa, Ethiopia

## Module for Distance Education

### ሐዲስ ኪዳን

### የዮሐንስ ወንጌልና ራእይ

2016 E.C

# ክፍል ሁለት

## የዮሐንስ ወንጌል

### ጸሐፊው

የ4ኛው ወንጌል ጸሐፊ ከ12ቱ ሐዋርያት አንዱ የሆነውና ጌታ ይወደው የነበረው ደቀመዝሙር ነው፡፡ ጌታ ይወደው የነበረው ደቀመዝሙር እንደጻፈው በወንጌሉ መጨረሻ /በም.21÷20-24/ ላይ ተገልጧል፡፡ ጌታ ይወደው የነበረው ደቀመዝሙር / ፍቁረ እግዚእ/ ደግሞ « ዮሐንስ» እንደሆነ በዓለም ቤተክርስቲያን ትውፊት ከጥንት ጀምሮ የታመነ ነው፡፡ ጐርጐርዮስ ዘእንዚናዙ በቀኖና መጽሐፉ ውስጥ የዚህን የ4ኛው ወንጌል ጸሐፊ « ታላቁ ሰባኪ ዮሐንስ ወልደ ነጐድጓድ» ብሎ ይጠራዋል፡፡ ወልደ ነጐድጓድ የሚለውን ቅጽል ለዮሐንስ የሰጠው ጌታችን እንደሆነ በወንጌል ተገልጧል ይህ ዮሐንስ የዘብዴዎስ ልጅ የትልቁ ያዕቆብ ወንድም ነው፡፡ በግእዝ ሐ.ኪ. ለወንጌሉ የተሰጠው ርእስ የዮሐንስ ወንጌል ጸሐፊ ከ12ቱ ሐዋርያት አንዱ የሆነው ፍቁረ እግዚእ ዮሐንስ ወልደዘብዴዎስ መሆኑን ሲገልጥ፡-

« ብሥራተ አብ ትሩፍ ረድእ ተናጋሪ በመለኮት ዮሐንስ ወልደ ዘብዴዎስ ፍቁረ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ » ይላል ለዚህ ወንጌል ትርጓሜ የተሰጠው መደምደሚያ ደግሞ፡-

« መልዓ ጽሕፈተ ብሥራቱ ለዮሐንስ ሐዋርያ ወልደ ዘብዴዎስ አሐዱ እምአሠርቱ ወክልኤቱ ሐዋርያት» ይላል፡፡

### ስሙ

« ዮሐንስ ማለት ጸጋ እግዚአብሔር ማለት እንደሆነ ብዙዎች መዝገበ ቃላቶች ይናገራሉ፡፡ ትርጓሜ ወንጌል ግን ዮሐንስ የሚለውን ስም ሲተረጉም «ዮሐንስ ማለት ፍስሐ ወሐሴት ማለት ነው፤ ወብዙኃን ይትፌስሑ በልደቱ እንዲል » ይላል. /ማቴ.10÷3 እና ሉቃ.1÷13:14 ትርጓሜውን

ተመልከት / ይህም የስሙ ምስጢራዊ ትርጉም ነው:: ዮሐንስ ዋና መጠሪያ ስሙ ሲሆን በተጨማሪ ግን በተለያየ ምክንያት የተሰጡት ብዙ የቅጽል ስሞች አሉት::

1. **ፍቁረ እግዚእ** :- ዮሐንስ በዚህ ስም የተጠራው በራሱ ወንጌል ውስጥ ነው/13÷23፤19÷26፤20÷2፤21÷20/ ወንጌሉን ሲጽፍ ራሱን ዮሐንስ ከማለት ይልቅ ፍቁረ እግዚእ /ጌታ የሚወደው/ብሎ የጠራው ስለትህትና እንደሆነ ብዙዎች ይናገራሉ:: እዚህ ላይ «ጌታ የሚወደው » ሲል ጌታ ሌሎቹን የማይወድ ሆኖ አይደለም:: በዚህ ዓለም ያሉትን ወገኖቹን የወደዳቸውን እስከ መጨረሻው እንደወደዳቸው በዚሁ በዮሐንስ ወንገል ተመዝግቧል /13÷1:34፤15÷12/ ነገር ግን ዮሐንስን ለይቶ « ጌታ የሚወደው» ያለው አንድ መምህር ከተማሪዎቹ መካከል በጠባዩ መልካም በትምህርቱ ጉበዝ የሆነውን ለይቶ እንደሚወደው ዓይነት ነው እንጂ በመሠረታዊ ፍቅሩ አድልቶ አይደለም::
2. <u>ወልደ ነጐድጓድ</u> ዮሐንስን «ወልደ ነጎድጓድ» ብሎ የጠራው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው:: ይህ ስም የተሰጠው ለእርሱ ብቻ ሳይሆን ለወንድሙ ለያዕቆብ ጭምር ነው:: በአራማይክ ቋንቋ « <u>ቦአኔርጌስ</u>» ተብለዋል:: ይህም ደቂቀ ነጎድጓድ / የነጎድጓድ ልጆች/ ማለት ነው/ ማር.3÷17 ተመልከት/

   ቦአኔርጌስ የሚለው ይህ ስያሜ የሚያመለክተውን ነገር በተመለከተ ከሚነጋገሩት አስተሳሰቦች ሁለቱን ቀጥለን እንመለከታለን::

   ሀ. ሁለቱ ወንድማማቾች ዮሐንስና ያዕቆብ የነበራቸውን የችኩልነት ጠባይ የሚያመለክት ስያሜ ነው የሚሉ አሉ::/ የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት ተመልከት/ ለምሳሌ በሰማርያ ክርስቶስን ያልተቀበሉትን ሰዎች እንዲጠፉ ለማድረግ፣ በክብሩ ጊዜ በክርስቶስ በግራውና በቀኝ ለመቀመጥ፣ ሲቸኩሉ እንመለከታለን/ ሉቃ. 4÷54፤ማር.10፤37:38/ ነጎድጓድ የሚታየውና ድምጹ የሚሰማው በጣም በፍጥነት እንደሆነ ሁሉ እነርሱም በችኩልነታቸው ደቂቀ ነጎድጓድ ተብለዋል::

   ለ. አምፊሎክዩስ ዘኢቆንዮን የቅዱሳን መጻሕፍትን ቁጥር በተናገረበት ቀኖናው ውስጥ ስለ ዮሐንስ «ወልደ ነጐድጓድ» መባል ሲናገር በጊዜ ቅደም ተከተል 4ኛን ከትምህርተ መለኮት አንጻር ግን 1ኛ ዮሐንስን ቁጠር፤ ምክንያቱም እኔም ወልደ ነጎድጓድ ብዬ በግልጥ እጠራለሁ:: ከሁሉም በላይ ስለቃለ እግዚአብሔር በከፍተኛ ምስጢር ድምጹን አሰምቷልና::» ብሏል::
3. ታአገሉለጉስ /ቴዎሎጎስ/ ቴዎለሉጎስ ማለት ነባቤ መለኮት ማለት ነው:: ወንጌሉን ሲጽፍ የኢየሱስ ክርስቶስን መለኮታዊነት አጉልቶና አስፍቶ ስለጻፈ የተሰጠው ስያሜ ነው:: «ቃለ እግዚአብሔር ነበር» ብሎ የቃልን እግዚአብሔርነት የገለጠ እርሱ ነው:: በሚጽፈው ታሪክ ሁሉ ኢየሱስ ክርስቶስ ከሰማይ መውረዱን ይናገራል:: ታምራቶችን በመጻፍም አምላክነቱን ይገልጻል:: /1÷1፤3÷13፤9÷3:34፤11÷4:25/ ጎርጎርዮስ ዘእንዚናዙም በኋላ ዘመን ተንሥቶ ትምህርተ መለኮትን በጥልቀት ስላስተማረ በዚህ ቅጽል ነባቤ መለኮት ተብሎ ተጠርቷል::

## ቤተሰቡ

ዮሐንስ አባቱ ዘብዴዎስ እንደሚባል የሐዋርያትን ስም ዝርዝር ከሚናገሩት ከ4ቱ ጥቅሶች ሁለቱ ይገልጣሉ:: እነርሱም 1/ማቴ.10÷2 እና 2 ማር.3÷17 ናቸው:: በተጨማሪም ማር.10፥35 ይህንነው በግልጽ ያስፈዳል እናቱ ደግሞ « ሰሎሜ» የተባለችው ሴት ሳትሆን አትቀርም የሚሉ አሉ:: ለዚህም የሚያቀርቡት ምክንያት ይህቺ ሴት ጌታ በተሰቀለ ጊዜ ከገሊላ ጀምሮ ከተከተሉት አንዷ መሆኗን በመግለጥ ማርቆስ ሰሎሜ ብሎ ሲጠራት ማቴዎስ ግን « የዘብዴዎስ ልጆች እናት» ብሎ ጠርቷታል:: የሚል ነው:: / ማቴ. 27÷56 እና ማር.15÷41ን አስተያይ:: / በትርጓሜ ወንጌል ግን የዘብዴዎስ ልጆች እናት ማርያም ባውፍልያ እንደምትባል ተገልጧል:: /ማቴ.20÷20 ትርጓሜዉን ተመልከት/

የዘብዴዎስ ልጆች እየተባሉ የሚጠሩት ያዕቆብና ዮሐንስ እንደሆኑ ተገልጧል:: ያዕቆብ ለዮሐንስ ታላቅ ወንድሙ እንደሆነ ይነገራል:: ስማቸው ተከታትሎ በተጠራበት በብዙዎቹ ጥቅሶች በቅድሚያ የሚጠራው ያዕቆብ መሆኑ ይህን ሊጠቁም ይችላል:: ማር.3÷17፤ሉቃ.6÷14/ የዮሐንስ ቤተሰዎች ይተዳደሩ የነበረው ዓሣ በማጥመድ እንደነበርና ዮሐንስም ከመጠራቱ በፊት ከወንድሙ ከያዕቆብ ጋር አባታቸው ዘብዴዎስን እያጋዘ ዓሣ ያጠምድ እንደነበር ተመዝግቧል/ማቴ.4÷21/

## መጠራቱ:

የዮሐንስ የመጠራቱ ታሪክ በግልጽ የተመዘገበው በማቴዎስና በማርቆስ ወንጌላት ነው/ ማቴ.4÷21:22፤ማር.1÷19:20/ የተጠራውም ከወንድሙ ከያዕቆብ ጋር ነው:: ከመጠራቱ በፊት የስምዖን ጴጥሮስ ጓደኛ ነበር /ሉቃ.5÷10/ ኢየሱስ ክርስቶስ የስብከት ሥራውን እንደጀመረ በቅፍርናሆም ከተማ በገሊላ አጠገብ ሲመላለስ 4 ደቀ መዛሙርቱን ጠርቷል:: ሁለቱ ጴጥሮስና ወንድሙ እንድርያስ ሲሆኑ ሁለቱ ደግሞ ያዕቆብና ወንድሙ ዮሐንስ ናቸው:: ሁሉም ዓሣ አጥማጆች ነበሩ:: ጌታ ጴጥሮስና እንድርያስን ተከተሉኝ ብሎ ከጠራ በኋላ ከዚያ አለፍ ብሎ ያሆቆብና ዮሐንስን ከአባታቸው ከዘብዴዎስ ጋር በታንኳ ውስጥ ሆነው መረባቸውን ሲያበጁ አየ:: እነርሱም ጠራቸው ወዲያውም ታንኳይቱንና አባታቸውን ትተው ተከተሉት::

በዮሐ.1÷35-40 ላይ እንደተገለጠው ጌታ ከጠራቸው ከሁለቱ የመጥምቁ ዮሐንስ ደቀ መዛሙርት አንዱ የጴጥሮስ ወንድም እንድርያስ እንደሆነ ተገልጧል:: ስሙ ያልተገለጠው ሌላው ደቀ መዝሙር ደግሞ ዮሐንስ ወልደዘብዴዎስ እንደሆነ ትርጓሜ ወንጌል ይናገራል እንዲህ ሲል::

« ወበሳኒታ ካዕበ እንዘይቀውም ዮሐንስ ወክልኤቱ እም አርዳአሁ በነጋው ዮሐንስ ከሁለቱ ደቀመዛሙርቱ ጋር ቆሞ ሳለ ሐተታ / ዮሐንስና እንድርያስ ናቸው» / 1÷35 ትርጓሜውን ተመልክት. . . / የራሱን ስም ያልገለጠው በዚህ ክፍል ውስጥ እርሱ ነገር ስለሌለው እንደሆነ ትርጓሜ ወንጌል ጨምሮ ገልጧል /1÷40/

ይህም ከሆነ ዮሐንስ በገሊላ ባሕር አጠገብ ከወንድሙ ከያዕቆብ ጋር የተጠራው ለሁለተኛ ጊዜ መሆኑ ነው::

በም.8፥14-24 ላይ ደግሞ ከእስጢፋኖስ ሞት በኋላ ከጴጥሮስ ጋር በሰማርያ ተገኝቶ በዚያ በፊልጶስ እጅ ለተጠመቁት ክርስቲያኖች ጸሎት አድርገው እጃቸውን በመጫን መንፈስ ቅዱስን እንዲሳደሩባቸው ተገልጧል።
ከዚህ ሌላ ግን በኢየሩሳሌም ጉባኤ ላይ መገኘቱን ከምንረዳ በቀር በሐዋርያት ሥራ ውስጥ ስሙ ተጠርቶ የተነገረለት ታሪክ የለም።

## በመልእክታት

ከመልእክታት ውስጥ የዮሐንስ ስሙ ተጠርቶ የምናገኘው በገላትያ መልእክት ውስጥ ነው። በዚህች መልእክት ውስጥ ከያዕቆብና ከኬፋ ጋር 3ኛ በመሆን « አዕማድ» ተብሎ ተጠርቷል። በተጨማሪም ለተገረዙት ሐዋርያ እንደሆነ ተገልጧል። /ገላ.2፥9/

## ያስተማረበት አገር

ዮሐንስ ስላስተማረበት አገር የአፖክሪፋ /አዋልድ/ መጻሕፍት ይናገራሉ። ለተገረዙት ሐዋርያት በመሆን ከጴጥሮስ ጋር የሰብከት ሥራውን በኢየሩሳሌምና በአካባቢው የጀመረው ዮሐንስ ወደ አንጾኪያ ሄዶ ያስተማረውም ከጴጥሮስ ጋር ነበር። እንደ ስንክሳር አገላለጥ ከኢየሩሳሌም እስከ አንጾኪያ በፈረስ 20 ቀን ያስኬዳል ነገር ግን እነርሱ በእግዚአብሔር ርዳታ ባንዲት ሌሊት ደረሱ። ዮሐንስ ቀደም ብሎ ወደ ከተማ ገባና ስለ ሐገሩ ጥናት ሲያደርግ የሐገሩ ሰዎች እጅግ ክፉዎች እንደሆኑ ተረዳ ምንም እንኳ ቢያዝንም ጴጥሮስ አጽናንቶ አደፋፈረውና ወደ ከተማ ገብተው በክርስቶስ ስም ወንጌል ሰበኩ። ከመምለኪያነ ጣዖት ብዙ መከራ ቢደርስባቸውም በአንጾኪያ ውስጥ ታምራትን እያደርጉ በስብከት የክርስቶስ ወንጌል ብዙ ህዝብ አሳምነዋል። ዮሐንስ ከዚህ ሌላ ያስተማረባት አገር ሉዶቂያ እንደሆነች ስንክሳር በተጨማሪ ይገልጣታል በከተማ አጠገብ ያለ ቂድሮስ የሚባል ወንዝ ሞልቶ የሀገሪቱን ብዙ ንብረት ባወደመ ጊዜ ዮሐንስ ከነጴጥሮስ ዘንድ ተልኮ ሄደና በታምራት የውኃውን ሙላት አቆመላቸው ወደ ከተማዋም ገብቶ ብዙ ታምራትን እያደረገ ወንጌልን ሰበከ። ካዩት ታምራትና ከሰሙት ትምህርት የተነሳ ብዙዎች አመኑ / ስንክ.ሐምሌ 5/ ይህ ታሪክ ግብረ ዮሐንስ /Acts of Jhon/ በተባለው መጽሐፍ ላይም ተመዝግቧል።

ዮሐንስ በህይወቱ መጨረሻ አካባቢ ያስተማረው በእስያ አገር በኤፌሶን ከተማ ነው። ከእርሱ አስቀድሞ በዚህች ከተማ ውስጥ በፊት ጳውሎስ በኋላም ጢሞቴዎስ እንዳስተማሩ ከመጽሐፍ ቅዱስ እንረዳለን። /የሐዋ.19፥1-41፤1ጢሞ.1፥9/ የቤተ ክርስቲያን ትውፊታዊ ታሪክ እንደሚያስረዳው ዮሐንስ ወደዚህች ከተማ የመጣው ከደቀ መዝሙር ከአብሮኮሮስ ጋር ነው። የስብከት ሥራቸውን በቀጥታ መጀመር ስላልቻሉ ሮምና በምትባል በአንዲት ልጅ / አሳዳጊ/ ሞግዚት / ቤት ውስጥ ባሮች ሆነው ገቡ። ከእለታት በአንድ ቀን ከምታሳድጋቸው ልጆች አንዱ የሀገረ ገዥው የዲዮስቆሮስ ልጅ ሞተ። ዮሐንስ ፀሎት አድርጎ በታምራት ከሞት ስላስነሳው ሮምና እና በዚያ የነበሩት ሁሉ ይህን አይተው በክርስቶስ አመኑ። ከዚያም በኤፌሶንና በአካባቢዋ ወንጌልን ለመስበክ ሰፊ በር ተከፈተለት። የተለያዩ ታምራትን በማድረግ ወንጌልን እያስተማረ ብዙዎችን በክርስቶስ እንዳሳመነ ይተረካል። / ስንክ ጥር 4/ ዮሐንስ በኤፌሶን በሚያስተምርበት ጊዜ ከኔሮን ቄሳር ቀጥሎ በሮም የነገሰው ድምጥያኖስ የራሱን ምስል አሰርቶ እንዲሰገድለት ወደ ኤፌሶን ልኮ እንደነበርና ዮሐንስ ከምእመናን ጋር ሆኖ ይህን ድርጊት እንደተቃወመ በቤ.ክ.ታሪክ ተመዝግቧል።

ዮሐንስ ይህን ተቃውሞ በማትረቡ ወደ ሮም ተወሰደ ከተፈረደበት በኋላ በመንግሥት ላይ ያመጹ ሁሉ በሚታሰሩበት በደሴተ ፍጥሞ እንዲታሰር ተደረገ። በዚያም ሳለ በአዲስ ኪዳን የመጨረሻ መጽሐፍ ውስጥ የተመዘገበውን ራዕይ አየ።

## ዕረፍቱ

ስለ ሐዋርያው ዮሐንስ የመጨረሻ ሕይወት ሁለት የተለያዩ አምለካከቶች አሉ።

1. በዮሐ. 21፥20-23/ ላይ የተጻፈውን ጌታ እስከመጣ ድረስ ይኖር ዘንድ ብወድስ ምን አግዶህ? « ብሎ ለጴጥሮስ የመለሰለትን ቃል በማቴ.16፥28 ላይ ከተነገረው ቃል ጋር በማያያዝ ዮሐንስ ሞትን አልቀመሰም የሚሉ አሉ።
2. በማቴ.20፥22:23 እና በማር.10፥38:39 የተጻፈውን ቃል በመጥቀስ ዮሐንስ የጌታን የሞት ጽዋን ጠጥቷል፣ የሞትን ጥምቀት ተጠምቋል፤ በግልጽ አነጋገር « ሞትዋል» የሚሉ አሉ። ጌታም « እስከመጣ ድረስ እኖር ዘንድ ብወድስ? አለ እንጂ « አይሞትም» አላለም። ትርጓሜ ወንጌል ዮሐ.21፥23 ላይ የተጻፈውን ይህን ቃል ሲተረጉም « ሞትዋል» ይላል ። ሌላም ትውፊት ዮሐንስ በ101 ዓመቱ በኤፌሶን እንደሞተና በዚያም እንደተቀበረ ይናገራል። ማትያስ የተባለው የቤተ ክርስቲያን አባትም በበኩሉ ዮሐንስ ወንጌላዊ በአይሁድ ተወግሮ እንደሞተ መዝግቧል።

- <u>ምሳሌው</u>

ዮሐንስ ከ4ቱ እንስሶች መካከል « በገፀ ንስር» ይመሰላል መቅድመ ወንጌል በ3ኛው ጉባኤ መጨረሻ ላይ 4ቱ ወንጌላውያን እያንዳንዳቸው የሚመሰሉባቸውን ምሳሌዎች ለይቶ በተናገረበት ክፍል ዮሐንስ በገፀ- ንሥር እንደሚመሰል ይናገራል። የትርጓሜ ወንጌል የታሪክ አምድ ደግሞ ዮሐንስ በገፀ ንሥር ለመምሰሉ ሁለት ምክንያቶች ይናገራል። እነርሱም፦

1. ንስር በእግሩ ይሽከረከራል በክንፉ መጥቆ ይበራል። በእግር እንዲሽከረከር እርሱ እንደ ወንድሞቹ ወልደ እጓለ እምሕያው ወረደ እምሰማይ እያለ ይጽፋል። በክንፍ መጥቆ እንዲበር እርሱም አካል ከህልውና ተገልጦለት « ቀዳሚሁ ቃል» ብሎ ተናግሮአልና፡
2. የንስር አይኑ ጽሩይ ነው። ሽቅብ ወጥቶ ረቦ ቁልቁል በተመለከተ ጊዜ የለናፍጭ ቅንጣት ያህል ሥጋ ብትሆንም አትሰውረውም ያችን አንስቶ ይመገባታል። እርሱም አካል ከህልውና ተገልጦለት ንጽሐ ሥጋ ንጽሐ ነፍስ ንጽሐ ልቡና ተሰጥቶት ቀዳሚሁ ቃል ብሎ ተናግሮአልና የሚሉ ናቸው።

## <u>የተጻፈበት ቦታ፣ ቋንቋና ዘመን፣</u>

ዮሐንስ ወንጌሉን የጻፈው ራእዩን ባየበትና በጻፈበት በኤጅያን ባሕር ውስጥ የምትገኘው በፍጥሞ ደሴት ውስጥ እንደሆነ የሚናገሩ ታሪኮች አሉ። ስንክሳር ስለዚህ ሲገልጥ ወጸሐፈ ወንጌለ ወአቡቀለምሲስ ውስተ ደሴተ ፍጥሞ» ይላል። የመቅድመ ወንጌል ተርጓሜና ወንጌል የታሪክ ዓምድ ግን ስለ ወንጌላት ጽሕፈተ ሀገር በተናገሩበት ክፍል የዮሐንስ ወንጌል የተጻፈበት ሐገር ኤፌሶን እንደሆነ ይገልጣሉ።

የጻፈበትም ቋንቋ « ፅርዕ» ፣ ዘመኑም ጌታ ካረገ በ30 ዓመት ኔሮን ቄሳር በነገሠ 7ተኛው ዓመት ተፈጽሞ 8ኛው ዓመት ሲጀምር እንደሆነ ጨምረው ገልጠዋል:: በዮሐንስ ወንጌል ትርጓሜ መደምደሚያ ላይ ይህን በተመለከተ ያሰፈረው ቃል በግዕዙ እንዲህ ይላል::

« መልዓ ጽሕፈተ ብሥራቱ ለዮሐንስ ሐዋርያ . . . ዘፀሐፎ በልሳ ዩናኒ ለሰብዓ ሀገረ ኤፌሶን እምድህረ እርገቱ ለእግዚእነ በሥጋ ውስተ ሰማይ በ30 ዓመት ወበ ሰባእቱ ዓመት መንግሥቱ ለኔሮን ቄሳር ንጉሠ ሮም»::

በዚህ ትውፊት የተገለጠው የዩሐንስ ወንጌል መዋዕለ ጽሕፈት ወደ አመተ-ምሕረት ሲለወጥ:-

- ከጌታ ዕርገት በፊት - 33 ዓመት
- ከጌታ ዕርገት በኋላ - 30 ዓመት

ድምር 63 ዓመት ይሆናል

ዘመናውያን ሊቃውንት ግን ዮሐንስ ወንጌሉን የጻፈው ወደ ሕይወቱ መጨረሻ አካባቢ በ96 ዓ.ም ገደማ እንደሆነ ይናገራሉ:: ይህም ከሆነ ከጌታ እርገት በኋላ በ60 ዓመት በላይ ቆይቶ ጽፎታል:: ማለት ነው:: ያም ሆነ ይህ የዮሐንስ ወንጌል የተጻፈው ሦስቱ ሲኖቲክ ወንጌላት ከተጻፉ በኋላ ብዙ ቆይቶ ነው::

## የተጻፈላቸው ሰዎች

ዮሐንስ ወንጌሉን የጻፈላቸው ሰዎች የኤፌሶን ክርስቲያኖች ናቸው:: ይህም በወንጌሉ ትርጓሜ መደምደሚያ ውስጥ በግልጽ ተነግሮአል:: በዮሐ. 20÷31 ላይ የሚገኘው ቃል ደግሞ ወንጌሉ ለኤፌሶን ሰዎች እንደተጻፈ ባይገልጥም የተጻፈላቸው የተወሰኑ ሰዎች እንደነበሩ ይጠቁማል:: ዮሐንስ ወንጌሉን የጻፈው ራእዩን ባየበት ወቅት ከሆነ በዚያ ጊዜ የነበረውን የኤፌሶንን ቤተ ክርስቲያን ሁኔታ ከራእየ ዮሐንስ ማወቅ እንችላለን:: በራእ.2÷1-7 ለኤፌሶን ቤተክርስቲያን መልአክ / አለቃ/ የተላለፈ መልእክት እናገኛለን:: ከዚህም መልእክት እንደምንረዳው የኤፌሶን ሰዎች ሐዋርያት ሳይሆኑ ሐዋርያት ነን የሚሉትን ሐሰተኞች መርምረው ስላወቋቸው ካለመቀበላቸው በላይ ክፉ ትምህርታቸውንና ሥራቸውን ጠልተዋል:: ነገር ግን ቀደም ሲል ለእምነታቸው የነበራቸውን ጽኑ ፍቅር ትተው ነበር:: በዚህ ሁኔታ ውስጥ ሳሉ በይዞታው ከሦስት ወንጌላት ለየት የሚለውን ይህን 4ኛውን ወንጌል ጻፈላቸው::

## የተጻፈበት ዓላማ

የዮሐንስ ወንጌል የተጻፈበት ዓላማ በወንገሉ ውስጥ በግልጽ ተነግሯል:: እርሱም እንዲህ ይላል:- « ኢየሱስም በዚህ መጽሐፍ ያልተጻፈ ብዙ ምልክት በደቀ መዛሙርቱ ፊት አደረገ፤ ነገር ግን ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ ታምኑ ዘንድ አምናችሁም በስሙ የዘላለም ሕይወት ይሆንላችሁ ዘንድ ይህ ተጽፏል» / ዮሐ.20÷30:31/

ከዚህ ጥቅስ እንደምንረዳው የዮሐንስ ወንጌል ዓላማዎች ሦስት ናቸው

1. ኢየሱስ እርሱ ይመጣል ተብሎ ይጠበቅ የነበረው ክርስቶስ እንደሆነ ለመግለጥ ነው:: 1÷16:20:24:42፤ 4÷25:26:29:42፤7÷25-27:40-44፤10÷24:25
2. ኢየሱስ እርሱ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ በተለያዩ ማስረጃዎች ለመግለጥ ነው::

/ 1÷34:50 ፤ 3÷6-18 ፤ 5÷18-26 ፤ 6÷69 ፤ 9÷35 ፤ 10÷36 ፤ 11÷4:27 ፤ 16÷27:28 ፤ 17÷2 ፤ 19÷7::/

3. የዘላለም ሕይወት የሚገኘው ወልድን በማመን መሆኑን ለማስተማር ነው /3÷15:16:36 ፤ 5÷24:39 ፤ 6÷40:43:54 ፤ 10÷10:28 ፤ 11÷27 ፤ 12÷25:50 ፤ 14÷6 ፤ 17÷3::/

- የዮሐንስ ወንጌል የኢየሱስ ክርስቶስን ታሪክና ትምህርት ሲናገር ማንነቱን በመግለጥ ላይ ያተኩራል:: የኢየሱስ ክርስቶስ ማንነት ሲገልጥም የተለያዩ ምስክሮችን በማቅረብ ነው:: በዚህ ወንጌል ውስጥ የክርስቶስን ማንነት የሚመሰክሩ ሰባት ምሥክሮች ተጠቅሰዋል::

1. የአባቱ ምስክርነት /5÷34-37 ፤ 8÷18::/
2. የራሱ የወልድ / የክርስቶስ / ምስክርነት / 8÷18:23:58::/
3. የመንፈስ ቅዱስ ምስክርነት /15÷26 ፤ 16÷12-14/
4. የሥራዎቹ ምስክርነት /5÷36 ፤ 10÷25/
5. የቅዱሳን መጻሕፍት ምስክርነት /5÷39-46/
6. የመጥምቁ ዮሐንስ ምስክርነት /1÷7 ፤ 5÷33-35/
7. የተማሪዎች ምስክርነት /15÷27 ፤ 19÷35/

- ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የራሱን ማንነት ያስተዋወቀባቸው ሰባት ቃላት በዚህ ወንጌል ውስጥ ይገኛሉ፤ እነርሱም « ሰባቱ እኔ ነኝ» ተብለው ይጠራሉ::

1. የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ /6÷35/
2. የዓለም ብርሃን እኔ ነኝ /8÷12/
3. የበጐች በር እኔ ነኝ /10÷7/
4. መልካም እረኛ እኔ ነኝ /10÷11/
5. ትንሣኤና ሕይወት እኔ ነኝ / 11÷25/
6. መንገድና ሕይወት እውነት እኔ ነኝ /14÷6/ (መንገድና እውነት ሕይወትም እኔ ነኝ)
7. እውነተኛ የወይን ግንድ እኔ ነኝ /15÷1/

- ከዚህም ሌላ በዮሐንስ ወንጌል ስለኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅነት / አምላክነት/ የመሰከሩ ሰባት ሰዎችን እናገኛለን:: እነርሱም:-

1. መጥምቁ ዮሐንስ /1÷29-36/
2. እንድርያስ /1÷41-42/
3. ፊልጶስ /1÷46/
4. ናትናኤል /1÷50/
5. ጴጥሮስ /6÷68-69/
6. ማርታ /11÷27/
7. ቶማስ /20÷28/ ናቸው::

- ጌታ ያደረገው የመጀመሪያው አንጽሖተ ቤተ መቅደስ /2÷13-25/
- የዘላለም ሕይወት የሚገኘው የእግዚአብሔርን ልጅ በማመን እንደሆነ የጌታ እና የመጥምቁ ዮሐንስ ትምህርት /3÷1-36/
- ኢየሱስ ክርስቶስ በሰማያዊ /4÷1-42/
- ኢየሱስ በቃና ዘገሊላ ያደረገው ሁለኛው ታምር /4÷43-54/

4. በሁለኛው የማስተማር ዓመቱ ያደረጋቸውና ያስተማራቸው ነገሮች /5÷1-6÷71/
   - የ38 ዓመቱን በሽተኛ በፈወሰ ጊዜ ያስተማረው ትምህርት /5÷1-47/
   - ህብስት እንዳበረከተና ስለሥጋ ወደሙ ትምህርት እንደሰጠ /6÷1-71/
5. በሦስተኛው የማስተማር ዓመቱ ያደረጋቸውና ያስተማራቸው ነገሮች /7÷12-13/
   - በዳስ በዓል በኢየሩሳሌም ሳለ አይሁድ ሊይዙት ያደረጉት ሙከራ /7÷1-53/
   - በመቅደስ ያቀረቡለት የፈተና ጥያቄዎችና ጌታ የሰጣቸው መልሶች /8÷1-59/
   - ዘአውሩ ተወልደን ፈውሶ ሲያስተምር ሊይዙት ሲሉ ከእጃቸው እንደወጣ //9÷1-42/
   - አልዓዛርን ከሞት ካስነሳ በኋላ ሊገድሉት ተማከረው እንዳስፈለጉት /11÷1-57/
   - በቢታንያ በአልዓዛር ቤት ሳለ በዚያ መሆኑን አውቀው ሊያዩት እንደመጡ /12÷1-11/
6. በመጨሻው ሳምንት ያደረጋቸውና ያስተማራቸው ነገሮች /12÷12-21÷14/
   - ወደ ኢየሩሳሌም ሲገባ ሕዝቡ ዘንባባ ይዘው ሆሳዕና ብለው እየዘመሩ እንደተቀበሉት /12÷12-19/
   - ስለሞቱ የተናገራቸው ነገሮች /12÷20-50/
   - የፋሲካ እራት በበላበት ምሽት ያደረጋቸውና ያስተማራቸው ነገሮች /13÷1-17÷26/
   - ተይዞ በሊቀ ካህናቱና በጲላጦስ ፊት መመርመሩ/18÷1-19÷16/
   - መሰቀሉና መቀበሩ /19÷17-42/
   - ትንሣኤውንና ለተከታዮቹ የመገለጡ /20÷1-21÷14/
7. የመደምደሚያ ቃላት /21÷15-25/
   - ጌታ ለጴጥሮስ የሰጠው አደራ /2÷15-19/
   - ወንጌሉን ስለጻፈው ደቀመዝሙር የመጨረሻ ሕይወት ጌታ የተናገረው /21÷20-24/
   - ኢየሱስ በዚህ ወንጌል ከተጻፈው ሌላ ብዙ ነገር እንዳደረገ /21÷25/



## ራእየ ዮሐንስ

የጥጦስ፣ የሐሳዊመሲሕ፣ የምጸአት፣ የመንግሥተሰማያት ነገር ተገልጾለት ተናግሮታል በሐዲስ ኪዳን ውስጥ የሚገኝ ብቸኛ የትንቢት መጽሐፍ ነው።
ኢትዮጰያውያን ሲቃውንት ደረቅ ሐዲስ ብለው ይጠሩታል። በውስጡ የያዛቸው ወደ 300 የሚጠጉ ምሳሌዎችና እያንዳንዳቸው በውስጣቸው የያዙት ትርጓሜ መጽሐፉ ከሌሎች የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ልዩ ያደርጉታል።

## የመጽሐፉ ስም

በግዕዝ ራእዩ ለዮሐንስ አቡቀለምሲስ፦ በሕይወት እያለ ራእይ ያየ በአማርኛ የዮሐንስ ራእይ
በግሪክ አፓካሊርሲስ ማለት መግለጥ፣ የተሸሸገውን ማሳወቅ ማለት ነው በእንግሊዝኛ ሪቨሌሽን ተብሎ ይጠራል።

## የመጽሐፉ ጠቀሜታ /ዓላማ/

1. የእግዚአብሔር ፍጹም ፍቅር የተገለጠበት መጽሐፍ ነው።
2. በተስፋ የተሞላ መጽሐፍ ነው፦ የቅዱሳንን ዕንባ እንደሚአበስ
3. የድል መጽሐፍ ነው፦ በመጨረሻ ዲያብሎስን እንዴት ድል እንደሚአደርገው ይናገራል።
4. በመንፈስ የሚፈጸምን ሥርዓተአምልኮ የሚአሳይ መጽሐፍ ነው
5. የመንግሥተሰማያት መግለጫ መጽሐፍ ነው
6. የሰውን ፍጹም ድህነት የሚያሳይ መጸሐፈ ነው

## መጽሐፉን የጻፈው ማነው?

ራእየ ዮሐንስን የጻፈው ዮሐንስ ወንጌላዊ ነው።
ሊቃውንት መጽሐፉን ዮሐንስ ወንጌላዊ ለመጻፍያስቀመጧቸው መስረጃዎች

1. የመጽሐፉ ጸሐፊ የታናሽ እስያ አብያተክርስቲያናትን የሚያውቅና በአካባቢው ያገለገለ መሆኑን ራእዩ የስረዳል
2. በድምጥያኖስ ዘመነመንግሥት ወንጌላዊ ዮሐንስ ወደፍጥሞ ደሴት ተግዞ እንደነበርና በዚያም ራእዩን እንዳየ /ራእይ 1:9/ የቤተክርስቲያን ታሪክ ያስረዳል።
3. ምንም እንኳ በወንጌሉና በራእዩ መካከል ልዩነት ቢኖርም ሁለቱን መጻሐፍት ብቻ የሚአመሳስሏቸው ነገሮች አሉ። ለምሳሌ፡- በግ፣ ቃል፣ ድል፣ እውነት የሚሉት በሁለቱም መጻሕፍት ተደጋግመው ተገልጠዋል።
4. ስሙን ገልጦ የተናገረበት ቦታ ስላለ ለምሳሌ
   - ለባሪያው ለዮሐንስ /ራእ. 1:1/
   - እኔ ወንድማችሁ የሆንኩ ከእናንተም ጋር አብሬ የኢየሱስ ክርስቶስን ትዕግስት የምካፈል /ራእይ. 1:9/ ያለውንና ሌሎች ተመሳሳይ ሀሳቦችን በማንሳት የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ሊቃውንት ራእዩ የዮሐንስ ወንጌላዊ መሆኑን በትርጎሜአቸው አስረድተዋል።

**የት ተጻፈ?**

ወንጌላዊው ዮሐንስ በመጽሐፉ እንደገለጠልን /ራእ. 1:9/ ራእዩን ያየውም የጻፈውም በፍጥሞ ደሴት ነው።

**መቼ ተጻፈ?**

ቅዱስ ዮሐንስ በድምጥያኖስ ዘመን በተነሣው የክርስቲያኖች ስደት ተግዞ ከኢየሩሳሌም ጥፋት በኋላ በ95/96 አካባቢ ራእዩን እያየ የጻፈ መሆኑን ብዙዎቹ ሊቃውንት ተስማምተውበታል።

**ለማን ተጻፈ?**

ራእዩ የተጻፈው በቅዱስ ዮሐንስ ሀገረ ስብከት ውስጥ ሥር ለነበሩት ለሰባቱ የታናሽ እስያ አብያተክርስቲያናት ነው። ራእ. 1:11

አጠቃላይ መልእክቱ Zስት ክፍሎች እንዳሉት ይታያል።

**ምዕራፍ** አንድ መግቢያ ነው፡- ማለት ራእዩን ማን እንደገለጠው ለማን እንደተገለጠ፣ መልእክቱ ለነማን እንደሚላክ ራእዩ የት ቦታ እንደታየ ባጭሩ ይገልጻል።

ከምእራፍ 2-3 በታናሽ እስያ ለሚገኙት ለሰባቱ አብያተክርስቲያናት በየራሳቸው የተላከላቸውን መልእክት ይዟል።

ከምእራፍ 4-22 ለመላው ዓለም የተገለጠ መልእክተ ነው በተለይ ደግሞ ሐሳዊመሲሕ በሚነሣ ጊዜ ቤተክርስቲያን የሚደርስባትን ፈተና እና የመውጫውንም መንገድ ጽንዑንም /ቅዱሳን/ የሚያገኙትንም ዋጋ ይተነትናል።



**የራእየዮሐንስ ልዩ መገለጫዎች**

1. በምሳሌዎችና ምልክቶች የተሞላ ነው
   ራእዩ ጥልቅ ምሥጢርን የያዘ በመሆኑ ትርሙም ጥልቅና ሰፊ በመሆኑ ብዙ ምሳሌዎችና መልክቶች ተገልጠዋል።
2. የሁለት ዓለም መጽሐፍ ይባላል
   ዮሐንስ በራእዩ ፍጥሞ በምትባል ደሴት በመንፈስ ነበርኩ በማለት የገለጠውን በመያዝ ሊቃውንት ፍጥሞ ደሴት የተባለች ክርስቲያኖች ዝግጅት የሚአደርጉባት ይህች ዓለም ስትሆን በመንፈስ ነበርኩ ማለት ደግሞ ሰማያዊውን ሕይወታቸውን ያሳያል።
3. ዙፋን፡- በመጽሐፉ ውስጥ ዙፋን የሚለው ቃል 40 ጊዜ ያህል ተደጋግሞ ተጠቅሷል።
   ይህም ክርስቲያኖች መከራውን ሁሉ ታግሰው እስከመጨረሻው ቢጸኑ የሚያገኙትን ክብርና የኢየሱስ ክርስቶስን ዘለዓለማዊ ስልጣን ያስረዳል።
4. የፍትር አምላክ መሆኑን
   መጽሐፉን ሲጀምር በ3ኛው ምዕራፍ በአንተፊት የተከፈተ በር ሰጥቸሀለሁ ማንም ሊዘጋው አይችልም ይላል ራእ. 3:8
   እነሆ በደጅ ቆሜ አንኳኳለሁ ማንም ድምፄን ቢሰማ ደጁንም ቢከፍትልኝ ወደእርሱ እገባለሁ ከእርሱም ጋር እራት እበላለሁ ራእ. 3:20 የሚለው ተስፋ እግዚአብሔር ለሰው ያለውን ፍትር የሚአመለክት ነው

**ሰባት ቁጥር በራእየዮሐንስ**

በዮሐንስ ራእይ ተደጋግመው ከተገለጡት ነገሮች አንዱ 7 ቁጥር ነው

1. ሰባቱ አብያተክርስቲያናት /ራእ. 1:4፣1/ እነዚህ አብያተክርስቲያናት በ7ቱ መቅረዞች ተመስለዋል/ራፍ. 1፣12፣20/ ይህም 7 ቁጥር የፍጹምነት ማረጋገጫ ስለሆነ መልእክቱ ቤተክርስቲያንን ለፍጹም ክብር ለማብቃት የተላከ መሆኑን ከመግለጡም በላይ ኢየሱስ ክርስቶስ የማይጠፋ ብርሃን ሁና በውስጧ እንደሚአበራና የጨለማውን ዘመንም እንደሚያሻግራት ያመለክታል።
2. ሰባቱ መንፈሶች /ራእ. 1:4/ አንዳንድ ሊቃውንት ሰባቱ መንፈሶች ሰባቱ ሊቃነመላእክት ናቸው ሲሉ ሌሎቹ ደግሞ የመንፈስ ቅዱስን ፍጹም የሆነ ሀብት /ሥራ/ የሚአመለክት ነው ብለው ተርጉመዋል።
3. ሰባቱ የእሳት መብራቶች የሰባቱ ምሥጡራተ ቤተክርስቲያን ናቸው። ሌላው መንፈስ ቅዱስ ለሰው የሚሰጠው ፍጹም ሀብቱ ነው /ራእ. 5:1

4. ሰባቱ ቀንዶች /ራእ.5፡6/ ዮሐንስ በራእዩ በዙፋኑ ላይ ያየው በግ ሰባት ቀንዶች ነበሩት። ቀንድ የኃይል፣ የክብር፣ የስልጣን ምሳሌ ነው። በሥጋ ደካማ መስሎ የተገለጠው አማናዊ በግ ኢየሱስ ክርስቶስ ዲያብሎስን ድል ያደረገበት ኃይል የባሐርይው /ገንዘቡ/ እንደሆነ ያመለክታል

5. ሰባት ዓይኖች /5፡6/ ወልደአምላክ ኢየሱስ ክርስቶስ ማእምረ ኩሉ፣ ማእምረኅቡዓት መሆኑን ያመለክታል።

6. ሰባት ሽ ሰማዕታት /ሪእ. 11፡13/ ሁለቱ ነቢያት ኤልያስና ሄኖክ የሚሰጡትን ምስክርነት ሰምተው በማመናቸው በሐሳዊመስሕ የሚሰውትን ሰማዕታት በፍጹም ቁጥር እንዲህ አለ።

7. ሰባት እራሶች /ራእ.12፡3/ የተነሣው አውሬ ሰባት እራሶች የሉት መሆኑ ከዚያ በፊት ታይቶ፣ ተሰምቶ የማያውቅ ፍጹምና አሰቃቂ መከራ በቤተክርስቲያን ማምጣቱን መናገር ነው።

8. ሰባት ተራሮች /ራዕ.17፡9/ አመነዝራዋ ባቢሎን የተቀመጠችባቸው ተራራዎች ሰባት ናቸው። ይህም አያሌ የዓለም መሪዎችንና ኃያላን ሀገሮችን የሚአስከትለው የሐሳዊመሲሕ መንግሥት ነው።

**የመጽሐፉ አከፋፈል**

ራእየዮሐንስ በዘጠኝ ክፍሎች የተከፈለ ነው።

1. መግቢያ ራእ፡1-20
2. ለሰባቱ አብያተክርስቲያናት የተጻፉ መልእክቶች ራእ.2 እና 3
3. ሰባቱ ማኅተሞች /4፡1-8፡5/
4. ሰባቱ መለከቶች /8፡6-11፡18
5. የዓለም ክፉ ዘመናት /11፡19፡14፡20/
6. ሰባቱ መቅሰፍቶች /15፡1-16፡21/
7. ባቢሎንና አርማጌዶን /17፡1-19፡21/
8. የሺ ዓመት መንግሥትና የመጨረሻው ፍርድ /20፡1-22፡5/
9. ማጠቃለያ /22፡6-21/

ራእየዮሐንስን በምልዐት ማወቅ የሚቻለው በዓለም ፍጻሜ ብቻ ነው

ሪእየዮሐንስ የብዙ ተስፋዎች መጽሐፍ ነው ለምሳሌ

- የተከፈተ የገነት በር
- የማታልፍ መንግሥት
- ሰማያዊ መዝሙር



- የበጉ ሠርግ
- አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር
- ዘንባባ ይዞ ማመስገን
- እንባቸውን ያብሳል
- ከበጉ ጋር በጽዮን ይነግሣሉ
- የታረደው በግ ድል አድራጊነት
- የዲያብሎስ ድል መሆንና ወደጥልቁ መጣል የመሳሰሉት ይገኙበታል።

**ምዕራፍ 1**

በዚህ ምዕራፍ ዮሐንስ የኢየሱሱ ክርስቶስን የባሕርይ አምላክነት ማለትም፡- ቀዳማዊነቱን፣ ማእከላዊነቱንና፣ ደኃራዊነቱን ይጽፍና ከዚህም በተጨማሪ ዳግም ምጽአቱን ይጸፋል።

ከዚህ በመቀጠል ራእዩ የትና እንዴት እንደተገለጠለት ይጽፋል ይህንንም ራእይ ለ7ቱ አብያተክርስቲያናት ጻፍ ተብሎ እንደታዘዘ ይጽፋል።

**ምዕራፍ አንድ 20 ቁጥሮች ሲኖሩት በውስጡም**

1. የነበረው፣ ያለው ዳግመኛ የሚመጣው በማለት ዘለዓለማዊነቱን እና ፈራጅነቱን ይናገራል።
2. ስለሰባቱ መናፍስት፡- ይኸውም 7ቱ ሊቃነመላእክት፣ የመንፈስ ቅዱስ ፍጹም ሀብት፣ ተብሎ ተተርጉሟል።
3. የሙታን በኩር ይለዋል ይኸውም ሞትን ድል አድርጐ ስለተነሣ
4. የነገሥታት ገዥ ብሎታል ይኸውም ነገሥታትን ከመቃብር አስነሥቶ የሚገዛ ዘለዓለማዊ ንጉሥ መሆኑን ያስረዳል።
5. ካህናት አንድንሆን ሳደረገን ይላል። ክህነት ሁለት አይነት ነው።

   አንደኛው በመመረጥና በመሾም የሚገኝ ሲሆን

   ሁለተኛው ደግሞ በጥምቀት የሚገኝ የልጅነት አገልግሎት ነው
6. ከደመና ጋር ይመጣል ሲል፡-
   - በባሕርይ ክብሩ ሲሆን
   - በሥጋማርያም / በክበብ ትስብእት/
7. አልፋና ኦሜጋ ይለዋል፡-
   - አንድነት Zስትነት ገንዘቤ የሚሆን
   - አ.ል.ፋ. /ምህጻረ ቃል ሁኖ አ ማለት እግዚአብሔር አብ ል ማለት እግዚአብሔር ወልድ ፋ ማለት ደግሞ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ማለት ነው
8. የጌታ ቀን ያላት ዕለተ እሁድ ናት ብለው መምህራን ተርጉመዋል

9. 7ቱ የወርቅ መቀረዞች፡- ፊትሉ የሰውነታቸው፣ ወርቁ የንጽህናቸው እሳቱ የመከራቸው፣ ብርሃኑ የጸጋቸው ምሳሌ ነው፡፡
10. በወርቅ መታጠቂያ የታጠቀ፡- ዮሐንስ ጌታን በራእይ ሲመለከተው በወርቅ መታጠቂያ ታጥቆ ነው ይኸውም ነጹህባሕርይ መሆኑን መታጠቁ ትእምርተኃይል፣ ትእምርተተልእኮ፣ ተዋሕዶን ገንዘብ ማድረጉን መናገር ነው
11. ጠጉሩ እንደነጭ የበግ ጠጉር የሆነ ማለት ብሉየመዋዕል፣ ጽሩየ ባሕርይ መሆኑን ያስረዳል
12. ዓይኖቹ እንደእሳት ነበልባል ናቸው ሲል
    - ፍጥረታታን የሚአውቅ የሚጠብቅ ማለት ሲሆን
    - ዓይኖቹ የተባሉ ነቢያት፣ እግሮቹ የተባሉ ሐዋርያት፣ ቀሳውስተ፣ ዲያቆናት ናቸው
13. እግሮቹ የጋለ/የነጠረ/ ናስ ይመስላሉ ሲል ትእምርተ መዓት ትእምርተ በቀል ገንዘቡ የባሕርይው የሆነ ማለት ነው፡፡ ሌላው እግሮቹ የተባሉ ብሉይና ሐዲስ ናቸው፡፡
14. በቀኝ እጁ 7ቱ ከዋክብት ነበሩ ማለት 7ቱ ኤጲስ ቆጶሳት በስልጣኑ ይጠበቃሉ ማለት ነው፡፡
15. ከአፉ በሁለት ወገን የተሰለ ስለታም ሰይፍ ወጣ ማለት ኀዐና ሁሩ የሚልበት ስልጣን የባሐርይው ነው ማለት ነው፡፡
16. ፊቱ እንደሚአበራ ፀሐይ ነበር፡- ማለት ፀሐይ 3 ነገር አላት ክበብ፣ ብርሃን፣ ሙቀት በክበቡ አብ፣ በብርሃኑ ወልድ፣ በሙቀቱ መንፈስ ቅዱስ ይመሰላል፡፡ ስለዚህ አንድነት Zሰትነት ገንዘቡ የሚሆን ተብሎ ይተረጐማል፡፡
17. የሞትና የሲኦል መክፈቻ አለኝ ሲል
    - ሞትን ፣ መቃብርን የማሳልፍበት ስልጣን ገንዘቤ ነው፡፡
    - ሙቼ፣ ተቀብሬ ሞትን ድል አድርጌ ተነሥቻለሁ ሲል እንዲህ አለ፡፡

**ምዕራፍ 2 እና ምዕራፍ 3**

እነዚህ ምእራፎች በዮሐንስ አማካኝነት በሰባቱ የታናሽ እስያ አብያተክርስቲያናት በኩል በመላው ዓለም መልታ ለምትገኘው ቤተክርስቲያን እግዚአብሔር የገለጠውን ምስጢር እናያለን፡፡ እያንዳንዱ አጥቢያ ቤተክርስቲያን ጠንካራና ደካማ ጉን ነበረው የበረታው እንዲቀጥል ከደካሙ እንዲነጻ መልእክት ተልኮላታል፡፡ በዚህም መሠረት ስማቸውን በማስተደያ ጠንካራ ጉናቸው ደካማ ጉናቸው፣ መፍትሔው ፣ በዝርዝር ተቀምጧል፡፡

1. የኤፌሶን አለቃ ስሙ አርስጦን ደካማ ጉኑ የቀደመ ፍቅሩን መተው
2. የሴሜርኔስ አለቃ ስሙ ኄሬኔዎስ እስከሞት ድረስ የታመንክ ሁን
3. የጴርጋሞን አለቃ ስሙ ጋይዮስ የኒቆላውያንን ትምህርት የያዙ ሰዎች ባንተዘንድ አሉ
4. የትያጥሮን አለቃ ስሙ ሉክዮስ ኤልዛቤልን ዝም ብለሀታልና



ምዕራፍ 3

5. የሰርዴሲሶን አለቃ ስሙ አርስጦን ስም ህየው ነው አንተግን ሙተሀል
6. የፊልደልፊልያ አለተ ስሙ ድሜጥሮስ አክሊልህን/ ክብርህን/ ማንም እንዳይወስድብህ ያለህን አጽንተህ ያዝ
7. የሎዶቅያ አለቃ አረከቦስ በራድ ወይመ ትኩስ አይደለህምና

**ምዕራፍ 4**

**ከዚህ ቀጥለው የሉ ምእራፎች ዮሐንስ በራእዩ ስለአዲሲቱ ኢየሩሳሌም ስለመንግሥተሰማያትና በመጨረሻው ዘመን በቤተክርስቲያን ላይ ስለማደርሰው ፈተና ያያቸው ናቸው፡፡**

እነዚህ ራዕዮች 3ቱን የቤተክርስቲያን የጉዞ ምዕራፎች የሚአሳዩ Zስት ተከታታይ ራእዮች ናቸው፡፡

1. 7ቱ ማኅተሞች፡- እነዚህ ቤተክርስቲያን የሚአጋጥማትን ፈተና እና የታረደው በግ የሚአደርግለትን ጥበቃ እና መግቦት የሚአመለክቱ ናቸው
2. 7ቱ መለከቶች፡- እነዚህ ዓለም በንስሐ እንድትመለስ እግዚአብሐር የላካቸው መንቂያ ማስጠንቀቂያ ናቸው
3. 7ቱ መቅሰፍቶች፡- እነዚህ ደግሞ እግዚአብሔር በሰጣቸው ማስጠንቀቂያ አልመለስ ብለው ልባቸውን ያደነደኑትን ለመቅጣት ያመጣቸው ቁጣዎችና መዓቶች ናቸው፡፡

ምዕራፍ አራት አስራ አንድ ቁጥሮች ሲኖሩት በውስጡም

1. በሰማይ የተከፈተ በር፡- ማለት በሰማይ መዘጋት መከፈት ኑሮ ሳይሆን የልታወቀ ምስጢር ተገለጠ ይኸውም የ4ቱ ኪሩቤልና የ24ቱ ካህናተሰማይ ሁኔታ ታወቀ ማለት ነው፡፡
2. ዕንቁ ኢያስጲድና ሰርዲኖ፡- የክበሩ ደንጋዮች ናቸው ጽርየተባሕርዩን መናገር ነው፡፡
3. የወርቅ አክሊል ደፍተዋል፡- ማለተ ክብራቸውን መናገር ነው
4. የብርጭቆና የበረድ ባሕር፡- ይህም ማለት ሰው ሁሉ አምኖ በጥምቀት ክብሮ የመኖሩ ምሳሌ፡፡
5. ነጭ ልብስ ለብሰዋል፡- ማለት ጸጋቸውን ንጽህናቸውን መናገር ነው
6. ዓይንን የተሞሉ ናቸው፡- ማለት ኃላፍያትንና መጻዕያትን/ ያለፈውንና የሚመጣውን ነገር ሁሉ ያውቃሉ ማለት ነው፡፡

ምዕራፍ 5

ምዕራፍ 5፡14 ቁጥሮች ያሉት ሲሆን በውስጡም

**ምዕራፍ አስር**

**መዕራሸ አስራ አንድ ቁጥሮች ሲኖሩት በውስጡ**

1. ከሰማይ የወረደ ግሩም መልአክ የተባለ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ሰማያዊ መሆኑንና ልጅቹን ለሰማያዋ ክብር የሚአበቃ ስለሆነ እንዲህ አለ
2. ቀስተደመና ተጐናጽፎ፡- ማለት የባሕርይ ክብሩን ገንዘብ አድርጐ ማለት ነው።
3. እግሮቹ እንደእሳት አምዶች ናቸው፡- ሲል ኃይሉን፣ ብርቱነቱን/ትእምርተ መዓት/ ገንዘቡ መሆኑን ያስረዳል።
4. የተከፈተች ትንሽ መጽሐፍ፡- ማለት ምስጢረ ምጽአቱ በቃሉ ትነገራለች ማለት ነው።
5. አንድ እግሩን በየብስ፣ አንድ እግሩን በባሕር ላይ ሁኖ መታየቱ የየብስም የባሕርም አምላክ ነኝ ሲል ነው።
6. እንደአንበሣ ሲአገሳ መታየቱ፡- ቤተክርስቲያንን መርዳቱንና አጋንንትን ድል ማድረጉን ያስረዳል።
7. በማፂተም ዝጋው አትጻፈው አለኝ፡- ሲል ጊዜው አለመድረሱን ያስረዳል
8. ውሰድና ብላት ማለት ምስጢረ ምጽአትን እወቃት ማለት ነው

**ምዕራፍ 11**

**ምዕራፍ አስራ አንድ አሰራ ዘጠኝ ቁጥሮች ያሉት ሲሆን በውስጡ፡-**

1. የተለካ የተሰፈረ ቤተመቅደስ፡- የተባለ የምእመናን ሕይወት ነው። ትን ሕዝ 40:48፣ ከ30 ጊዜ በላይ ለክቷል።
2. ውድሞው በውጭ ያለው ለአሕዛብ ተሰጠ ማለት፡- የአሕዛብን ሥራ የሚሠሩ ሰዎች ተሰጠ ማለት ነው። ቅዱስ ጳውሎስ በ2ኛ ተሰሎ 2:4 ላይ ይነብር ቤተመቅደስ/ቤተእግዚአብሔር/ ይላል ከዚህ እንዳልገባ ዮሐንስ ይናገራል። እንደምን ነው ቢሉ ቅዱስ ጳውሎስ ቤተእግዚአብሔር ያለው ስመ እግዚአብሔር የሚጠራበትን የካህናቱን ቤት ነው እንጅ ነገር እንደዮሐንስ ነው ቤተእግዚአብሔር አልገባም።
3. አርባ ሁለት ወር፡- ያለው የሐሳዌመሲሕን ዘመነ መንግሥት ነው ትን ዳን ምዕ. 8 ላይ 2300 ቀናት ብሎታል Zስት ዓመት ከ6 ወር ማለት ነው
4. ማቅ የለበሱ ሁለቱ ምስክሮች የተባሉ፡- ኤልየስና ኄኖክ ናቸው። ሚል.4:5 ፣ ዘፍ.5:24። ዕፀዘይት፣ መቅረዞች ማለቱ በእግዚአብሔር ፊት የሚቆሙ የእግዚአብሐረ ባለሟሎች ለማለት ነው።
5. የእግዚአብሔር መቅደስ ተከፈተ ማለት፡- መንግሥተ ሰማያት ተሰጠች ማለት ነው። የመቅደሱ ታቦት ታየ ማለት፡- ህጉን የጠበቀች ምእመን ክብራ ታየች ማለት ነው።



6. መብረቅ ነጐድጓድ ሆነ ማለት፡- መቅሰፍተኃጥአን ታዘዘ፣ ህልፈተ ዓለም ሆነ ማለት ነው።

**ምዕራፈ 12**

**ምዕራፍ አስራ ስምንት ቁጥሮች ሲኖሩት በውስጡ**

1. ፀሐይን የተጐናጸፈችው ሴት የተባለች፡-
    - ቤተክርስቲያን ስትሆን
    - እመቤታችን ናት ብለው መምህራን ተርጉመዋል
2. ዘንዶው የተባለ ዲያብሎስ ነው። ዮሐንስ ዲያብሎስን ዘንዶ፣ አውሬ የቀደመው እባብ በማለት ይገልጸዋል።
3. 7ቱ እራሶች የተባሉ 7ቱ አርእስተኃጣውእ ሲሆኑ አስር ቀንዶች የተባሉ አሳማውን የሚአሰፈጽሙለት አስሩ ነገሥታት ናቸው
4. የሰማይን ከዋክብት እየሳበ ወደምድር ጣላቸው፡- የተባሉ ዲያብሎስ በወደቀ ጊዜ ከአርሱ ጋር ወደጥልቁ የተጣሉት አጋንንት ናቸው።
5. 1260 ቀናት የተባሉ 3 ዐመት ከ6 ወር የሐሳዌ መሲህ ዘመነ መንግሥት ወይም ኤልያስና ኄኖክ በዚህ ዓለም የሚአስተምሩበት ዘመን ነው።
6. ለሴቲቱ የተሰጧት ሁለቱ ክንፎች፡- ለምእመናን/ለቤተክርስቲያን / ምግባር ከሀይማኖት ሃይማኖት ከምግባር ሲሆን ለእመቤታችን ደግሞ ንጽሀሥጋ ንጸሀነፍስ ነው። ተብሎ ተተርጉሟል

**ምዕራፍ 13**

**ምዕራሸ አስራ ስምንት ቁጥሮች ሲኖሩት በውስጡ**

1. አውሬ ከባሕር ሲወጣ አየሁ ሲል አውሬ የተባለ ሐሳዌመሲሕ ነው ከባሕር ሲወጣ ማየቱ መንግሥቱ ገና ስላልተደላደለ ነው።
2. አስር ተንዶች ሰባት እራሶች አሉት ማለት 7ቱ እራሶች 1ኛ 7ቱ አርስተኃጣውእ ናቸው እነሱም፡-
    - ኀጢአተአዳም
    - ቅትለተ አቤል
    - ጥቅመ ሰናዖር
    - ኃጢአተሰዶም
    - ኃጢአተ እስራኤል
    - ቅትለተ ዘካርያስ
    - ሞተወልደ እግዚአብሔር ናቸው

    እነዚህ ሁሉ በእርሱዘመን ይሰራሉና ነው። ሌላው 7 ራሶች የተባሉ 7ቱ ሀገሮች ናቸው እነሱም ፋርስ ባቢሎን፣ ፅርዕ፣ ሜዶን፣ ግብፅ፣ ኢየሩሳሌምና ሮም ናቸው።

3. የስድብ ስም አለበት ማለት አምላክ ነኝ ይላልና ነብር ይመስላል ማለት መንግሥተፋርስ ገንዘቤ ነው ይላልና እግሩ እንደድብ ነው ማለት ድብ ከጅብና ከአንበሣ የሚወለድ እንስሳ ነው እሱም መንግሥተዳርዮስ ገንዘቤ ነው ይላልና።
4. አንዲቱ በሞት አወጋግ የተወጋች ናተ ቁስሉም ዳነ ማለት ኃጢአተ አዳም በሞተወልደ እግዚአብሔር ጠፍታ በሱ ጊዜ ትሰራለችና እንዲህ አለ።
5. ሌላ አውሬ ከየብስ ወጣ የተባለ፡- ሐሳዊኤልያስ ነው። ሁለት ቀንዶች የተባሉ ሐሳዊኤልያስና ሕሳዊ አብድዩ ናቸው።
6. 666 የሚለው ቁጥር፡- እንደማንኛውም ሰው 666 አስራው ያሉት ፍጡር መሆኑን ለማስረዳት ነው።

**ምዕራፍ 14**

**ምዕራፅ ሃያ ቁጥሮች ሲኖሩት በውሰጡም፡-**

1. በጉ በደብረጽዮን ቁሞ አየሁ ማለተ፡- በመስቀል ተሰቅሎ፣ ጠላቱን ድል አድርጐ ማየቱንና ምስጢረ ምጽአቱም የሚፈጸም በዚያ ነውና እንደህ አለ።
2. አስራ አራት እልፍ ከአራትሽ ህጻናት የተባሉ፡- በሰማዕትነት የሚሞቱትን በፍጹም ቀጥር እና በኄሮድስ ጊዜ የሞቱት ህጻናት ናቸው
3. እንግዳ ምስጋና የተባለ፡- ሰው አምላክ ሆነ፣ አመላክ ሰው ሆነ ያለው
4. ሌላ ሁለተኛ መልአክ የተባለ፡- ጌታ ነው። ኤልያስ፣ ዮሐንስ መጥምቅ ነው የሚሉም አሉ።
5. ሁለተኛ መለአክ ተከተለው ያለው፡- ኄኖክ፣ ሐዋርያት ናቸው
6. Zስተኛ መልአክ የተባለ፡- መጻሐፍት፣ እስከምጽአት የሚነሡ መምህራን ናቸው።
7. ስለታም ማጭድ የተባለ፡- ዓለምን የሚአሳልፍበት ስልጣን ነው።

**ምዕራፍ 15**

**ምዕራፅ ስምንት ቁጥሮች ሲኖሩት በውስጡ፡-**

1. ምየምትመስል ባህር የተባለች፡- መንግስተሰማያት ናት እመቤታችንም የሚሉ አሉ
2. እሳት የተቀላቀለባት፡- መለት የሚቀበሉት መከራና የሚአገኙት ክብር ነው።
3. በሰማይ ያለ መቅደስ ተከፈተ ማለት፡- የልታወቀ ምስጢር ተገለጠ ማለት ነው።
4. ብሩህ ልብስ ለብሰዋል ማለት ፀጋቸውን መናገር ነው
5. የወርቅ ዝናር ታጥቀዋል ማለት፡- በንጽህና ሁነው የሚሰጡት አገልግሎት /ምስጋና/ ምሳሌ ነው።

**ምዕራፈ 16**



**7ቱ መቅሠፍታት**

ይህ ምዕራፍ ሃያ አንድ ቁጥሮች ሲኖሩት በውስጡ

1. የመጀመሪያው መልአክ ጽዋውን በምድር ላይ አፈሰሰ ማለት በአይሁ ላይ የሚመጣውን መከራ መናገር ነው በምድር ማለቱ እስራኤል ዘሥጋ ናቸውና
2. ሁለተኛው በባሕር ላይ ማለት፡- አሕዛብ ናቸው
3. Zስተኛው በአፍላግ ፣ በአንቅዕት ላይ አፈሰሰ ማለት፡- ሐሰተኞች መምህራን የማአስተምሯቸው ኑፋቄዎች ፍልስፍናዎች ናቸው። ደም መሆኑ ተከታዮቹ በሙሉ ለሞት መብቃታቸው ነው።
4. አራተኛው ጽዋውን ወደፀሐይ አፈሰሰ ማለት፡- መምህራነ ወንጌል ካህናት ናቸው፡1 መሞታቸውን መናገር ነው።
5. አምስተኛው በሐሳዊመሲሕ ከተማ አፈሰሰ ማለት፡- ኃይሉ እየደከመ መሄዱን መናገር ነው።
6. ስድስተኛው በኤፍራጥስ ወንዝ ከወደ ምስራቅ የሚመጡ ነገሥታት መንገዳቸው ጥርጊያ ትሆን ዘንድ ማለት ብሐረብፁዐን ያሉ ሰዎች በመጨረሻ ዘመን እንደሚመጡ መናገር ነው።
7. ሰባተኛው ጽዋውን በነፋስ ላይ አፈሰሰ ማለት፡- ፍትሐእግዚአብሔር ተደረገ ማለት ነው።

**ምዕራፍ 17**

**ምዕራፅ አስራ ስምንት ቁጥሮች ሲኖሩት በውስጡ፡-**

1. በብዙ ውኃ ላይ የተቀመጠች ዘማ የተባለች፡- ባቢሎን ናት ቤተአይሁድ ሮም ብለው የተረጐሙ መምህራንም አሉ።
2. የስድብ ስም የተሞላበት ቀይ አውሬ የተባለ፡- ሐሳዊመሲሕ ነው።
3. አውሬው በገናንነት አለ፣ በገናንነት የለም ማለት፡- አለ የተባለ ከአዳም እስከክርስቶስ ሰው መሆን ድረስ ሲሆን የለም የተባለ ደግሞ ከክርስቶስ ሰው መሆን በኋላ ድል ተነስቶ ነው።
4. ከከተማ ነግZ ይወጣል ማለት፡- በሐሳዊመሲሕ ጊዜ እንደገና መነሣቱን መናገር ነው።
5. 7ቱ ነገሥታት፡- በየጊዜው የሚነሡትን በፍጹም ቆጥሮ ነው ሁለቱ መንግሥተሮም፣ መንግሥተ ተንባላት ናቸው።

**ምዕራፍ 18**

**ምዕራፅ ሃያ አራት ቁጥሮች ሲኖሩት በውስጡ፡-**

1. የባቢሎን ጥፋት፡- ፈወስናሃ ለባቢሎን ወኢተፈወሰት ኤር. 51፡9
2. ጸኑዕ ስልጣን ያለው መልአክ የተባለ፡- ጌታ ነው
3. መዕራፅ በአጠቃላይ የባቢሎን አወዳደቅ የሚናገር ነው

**ምዕራፍ 19**

**ምዕራብ ሃያ አንድ ቁጥሮች ሲኖሩት በውስጡ**

1. ወደሠርጉ ቤት እራት የተጠሩ ብፁዓን ናቸው፡- ማለት ለክብር የበቁ ማለት ነው።
2. መልአኩ አትስገድልኝ ማለቱ፡-
    - ዮሐንስ ከፍጹምነት መዓርግ ደርሶ ስለነበር ለትህትና ሲሆን
    - ዮሐንስ መልአኩ ጌታ መሰሉት የባሕርይ ስግደት ሊሰግድለት ስለነበር ከለከለውና ሁላችንም ለእግዚአብሔር እንስገድ አለው።
3. እምባላይ ፈረስ ማለት፡- ንጹሀባሕርይ መሆኑን ያስረዳል።
4. ዐይኖቹ ነደዕሳት ናቸው ማለት፡- ትእምርተበቀል፣ ትእምርተ መዓት ገንዘቡ የሚሆን ማለት ነው።
5. ደም የተረጨ ልብስ ማለት፡- ለሰው ብሎ መሞቱን ያስረዳል።

**ምዕራፍ 20**

**በዚህ ምዕራፍ ውስጥ አስራ አምስት ቁጥሮች ሲኖሩት በውስጡ፡-**

1. ከሰማይ የወረደ መልአክ የተባለ፡- ጌታ ነው
2. ሽሕ ዘመን አጋዘው ሲል፡- ሽ ዘመን የተባለ ዘመነወንጌል ፣ የፍርድ ቀን፣ ከምጽአት በኋላ ያለው ዘመን ነው ተብሎ ተተርጉሟል።
3. ከክርስቶስ ጋር ሽ ዘመን ይነግሣሉ ማለት፡- አድሮባቸው ይኖራል ማለተ ነው። ሽ ዘመን እንደላይኛው ይተረጉማል።
4. ጎግ፣ ማጎግ ማለት፡- ብዙ የብዙ ብዙ ንጉሡን፣ ሠራዊቱን፣ አይሁድ ተንባላት መምለክያነጣዖት ተብሎ ተተርጉሟል።
5. መጽሐፈሕይወት ተገለጠች ማለት፡- መጽሐፈ ሕይወት የተባለች ወንጌል ናት ተገለጠች ማለት ወንጌል ዋጋ ማስጠቷን መናገር ነው።

**መዕራፍ 21**

**ይህ ምዕራፍ ሃያ ሰባት ቁጥሮች ሲኖሩት በውስጡ፡-**

1. አደስ ሰማይና አዲስ ምድር የተባለች፡- መንግሥተሰማያት ናት።
2. እንባን ከዓይናቸው የርቃል ማለት፡- ዋጋቸውን ሰጥቶ ደስ ያሰኛቸዋል
3. ከሕይወት ውኃ መንጭ ይጠጣ ዘንድ እሰጠዋልሁ ማለት፡- በልጅነት የሚሰጥ ክብር የክብር ክብር እሰጠዋለሁ ማለት ነው።



4. አስራ ሁለቱ የከበሩ ድንጋዮች /እዕናቁ/ የ12ቱ ነገደ እስራኤል ምሳሌዎች ሲሆኑ 12ቱ ነገድ ደግሞ የ12ቱ ሐዋርያት ምሳሌዎች ናቸው።
    - ኢየስጲድ የሮቤል የጴጥሮስ
    - ሰንፔር ስምዖን እንድርያስ
    - ኬልቄዶን ይሳኰር ማቴወስ
    - መረግድ ይሁዳ ዮሐንስ
    - ሰርዶንክስ ሌዊ የዕቆብ ወ/ዘብዴዎስ
    - ሰርጽዮን ጋድ ያዕቆብ ወ/እልፍዮስ
    - ክርቲሎቤ ንፍታሌም በርተሎሜዎስ
    - ቢረሌ ዛብሎን ፊልጶስ
    - ወራውሬ ብንያም ናትናኤል
    - ክርስጵራስስ አሴር ቶማስ
    - ያክንት ዮሴፍ ታዴዎስ
    - አሜቴስጢኖስ ዳን ማትያስ

ዮሐንስ በራእዩ መንግሥተሰማያትን በ12ቱ እዕናቁ ተሰርታ አጊጣ ማየቱ ነቢያት፣ ሐዋርያት አንድ ሁነው መንግሥተ ሰማይ የመግባታቸው ምሳሌ ነው።

**ምዕራፍ 22**

**ምዕራፍ አስራ ስምንት ቁጥሮች ሲኖሩት በውስጡ**

1. የሕይወት ውኃ የሚፈስበት ወንዝ ማለት፡- በልጅነት ክብር የሚሰጥበት ማለት ነው።
2. ዕፀ ሕይወት ማለት፡- ሥጋው ደሙ፣ ቃለ እግዚአብሔር፣ ራሱ ኢየሱስ ክርስቶስ፣ መስቀል፣ መንግሠተሰማይ ተብሎ ተተርጉሟል።
3. ልብሳቸውን ያጠቡ ሰዎች ንዑዳን፣ ክቡራን ናቸው ማለት፡- ሰውነታቸውን ከኃጢአት የለዩ ማለት ነው።
4. 5ቱ ከለባት/ውሾች/ የተባሉ፡- አስማተኞች፣ ዘማውያን፣ ቀታልየን/ ነፍስገዳዮች/ ጣዖት አምላኪዎች፣ ሐሰተኞች ናቸው።

## ትክክለኛው መልስ ምረጥ

1.ከሚከተሉት አንድ ምዕራፍ ብቻ ያለው መልእክት የጻፈ ሐዋርያ ማን ይባላል?

ሀ. ቅ/ጴጥሮስ ለ. ቅ/ዮሐንስ ሐ ቅ/ይሁዳ መ. ቅ/ ያዕቆብ

2.ሦስት መልእክታት ያሉት ሐዋርያ ማን ይባላል

ሀ. ቅ/ያዕቆብ ለ. ይሁዳ ሐ. ዮሐንስ መ. ጴጥሮስ

3.የቅ/ጴጥሮስ ትልዱ ነገዱ ከ -------------------ነው?

ሀ. ከነገደ ሮቤል ለ. ከነገደ ይሁዳ ሐ.ከነገደሌዊ

4.ቅ/ጴጥሮስን ያስገደለው ቄሣር-------------------- ይባላል

ሀ. ኔሮን ቄሣር ለ. ጢባርዮስ ቄሣር ሐ. አውግስጦስ ቄሣር

5. ከ4ቱ አፍላጋት በፈለገኤፍራጥስ የሚመሰል ወንጌላዊ /ሐዋርያ /ማን ይባላል?

ሀ. ቅ/ሉቃስ ለ. ቅ/ዮሐንስ ሐ. ቅ/ማቴዎስ መ. ሁሉም

6. የጌታን ስነስቅለት ለመጀመሪያ ጊዜ ከለሜዳ አስታጥቆ የሳለ ወንጌላዊ /ሐዋርያ/ ------ይባላል

ሀ. ቅ/ሉቃስ ለ. ቅ/ዮሐንስ ሐ. ሀናስ መ. መ/የለም

7. የወንጌላዊ ዮሐንስ በዓለዕረፍት /የተሰወረበት/ ቀን መቼ ነው?

ሀ. ጥቅምት 4 ለ.ታህሳስ 4 ሐ.ጥር4 መ. ሁሉም

8. ወንጌላዊ ዮሐንሰ መልእክቱን የጻፈላት ሴት ማን ትባላለች?

ሀ. አውዶክሰያ ለ. ሮምና ሐ. ኤልዛቤል መ. መልስ የለም

9. ከወንጌላዊ ዮሐንሰ ጋር ብዙ መከራ በመቀበል ከሱ ጋራ የሴት አገልጋይ እስከመሆን ደርሶ የነበረ የዩሐንስ ደቀመዝሙር ማን ይባላል ?

ሀ.ፋጊር ለ. አብሮኮሮሰ ሐ. ያዕቆብ መ. ሁሉም

10.የያዕቆብ እኁሁ ለእግዚእነ በዓለዕረፍቱ መቼ ነው?

ሀ. ሰኔ 18 ለ .ሐምሌ 18 ሐ.ጥር 18 መ.መልስ የለም



## ማብራሪያ ስጥ

1. ሐዋርያው ያዕቆብ እኁሁ ለእግዚአነየጌታወንድም የተባለበት ምክንያቱ ምንድን ነው?የተባለበት ምክንያቱ ምንድን ነው---------
2. የያዕቆብ ወንድም ይሁዳ እናትና አባት ማን ማን ይባላሉ
3. ራእየዮሐንሰን የጻፈው ማነው ? ወንጌላዊ ዮሐንስ ወይስዮሐንስ አፈወርቅ ?
4. 7ቱ አርእስተኃጣውዕ የሚባሉ ማን ማን ናቸው ?
5. 5ቱ ከለባት /ውሾች/ የተባሉ እነማን ናቸው፡፡ ዘርዝር